# የፀረ-ሙስና ሕግና አፈፃፀም በኢትዮጵያ

**ጥናቱን ያከናወኑ ባለሙያዎች፡-**


ድልነሳው እስራኤል

ሙኡዝ ገ/ልዑል

ቴዎድሮስ ዳዊት

1.የፌዴራል የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀሎች በተመለከተ የመመርመርና የመክሰስ ስልጣን አለው፡፡ የኮሚሽኑ የመክሰስ የስልጣን ወሰኑ ደግሞ በመንግስት መስሪያ ቤቶችና በመንግስት የልማት ድርጅቶች የተወሰነ ነው፡፡ ነገር ግን ከሌሎች ሃገሮች ልምድ እንደታየው በሃገር ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሥርዓት ውስጥ ከፍተኛ ሚና በሚጫወቱ የግል ተቋማት ውስጥ የሚፈፀሙ የሙስናና ወንጀሎችን ለመከላከል የሚያስችል ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ነው፡

2. በሀገሪቱ የሙስና መከላከል ተግባራትን የሚመራ ተቋም መቋቋሙ ከፍተኛ አዎንታዊ ተፅዕኖ ያመጣ መሠረታዊ ጉዳይ ቢሆንም ከዚህ ጥናት መረዳት እንደሚቻለው የፌዴራል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን የአምስት አመት የማስቀጣት አቅሙ (conviction rate) 49.5 በሞቶ ሲሆን ይህም በአማካይ ሲሰላ 51.04 በሞቶ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከአመት አመት የማስቀጣት አቅሙ እየጨመረ የሄደ ሣይሆን አንዴ ከፍ አንዴ ዝቅ የሚል መዋዥቅ ይታይበታል፡፡ ስለዚህ ኮሚሽኑ ያሉበትን ችግሮች በመቅረፍ ይበልጥ ተጠናክሮ ወደ ተሻለ አሰራር መግባት ይኖርበታል፡፡

3. የሃብት ማሣወቅ የሕግ ማዕቀፍ መውጣቱና ተግባራዊ መሆን መጀመሩ ሙስናን ለመከላከል ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ይታመናል፡፡ በአሰራሩን አጠናክሮ መቀጠልና የተመዘገበ ሃብትና ንብረት ለህብረተሰቡ ይፋ የሚሆንበት አሰራር ማመቻቸት አስፈላጊ ነው፡፡

4.የብሄራዊ ቅንነት ሥርዓት / National Integrity System / በኢትዮጵያ የሙስና መከላከል ሥርዓት ውስጥ በጠንካራ መሠረት ላይ የተገነባ ባይሆንም ከሞላ ጎል እንዳለ ይታያል፡፡ በመሆኑም ይህን ሥርዓት በህግ የበላይነት እና የዴሞክራሲ ስርዓት ጋር በጠንካራ መሰረት ላይ ለመገንባት የስርዓቱ ዋንኛ መሠረቶች፣ ምሰሶዎችና የሚሠራባቸው መሠረታዊ መርሆዎች ሊጠናከሩ ይገባል፡፡ የብሔራዊ ቅንነት ሥርዓት አንዱና ዋነኛው የዴሞክራሲ ስርዓት መገለጫ እንደመሆኑ መጠን ሁሉም የሚመለከተው አካል በመሣተፍ የሚጠበቅበትን በጋራም በተናጥልም እንዲወጣ የተጠናከረ እንቅስቃሴ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

5. የመንግስትም ሆኑ ጉልህ ኢኮኖሚያዊ ሚና ያላቸው የግል ተቋማት አሰራራቸውን በየጊዜው በመፈተሽ ለሙስናና ብልሹ አሰራር ሊያጋልጡ የሚችሉ ሁኔታዎችን ቀድሞ ለመከላከልና ሲከሰትም ፈጣን ማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ በሚችሉበት ሁኔታ እንዲገኙ በዚህ መስክ የተጀመረውን ጥረት አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል፡፡

6. አለም አቀፋዊ የትብብር መድረኮችን ማጠናከር አገር ለቀው የሚጠፉ ተጠርጣሪዎችን ወደ ህግ ለማቅረብናና ከአገር ውጭ የሚያሸሹ ከሙስና የተገኙ ንብረቶችን ለመቆጣጠር ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል። የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የሚያወጡት የተጠርጣሪ ተይዞ ይቅረብ ሰነድ (arrest warrant) በሌሎች አገሮች ውስጥ ተፈፃሚ እንዲሆንና፣ በሌላኛው አገር ውስጥም ተጠርጣሪው ያስቀመጠው ንብረት ወይንም ገንዘብ ካለ ሃብቱን ፈልጎ ለማግኘት እና ከተገኘ በኋላም ተጠርጣሪው እንዳያንቀሳቅሰው በማድረግ ተግባር ላይ ተጠርጣሪው ወይም የሸሸው ንብረት የሚገኝባቸው አገሮች ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል። ስለሆነም ከተለያዩ አገሮች ጋር፣ በተለይም በአብዛኛው ተጠርጣሪዎች ይሄዱበታል ተብለው ከሚገመቱ አገሮች ጋር ስምምነት በመፈፀም የሙስና ሕጉን የማስፈፀም አቅም ማጠናከር ይቻላል።

7. በአገራችን የህግ ሥርዓት ውስጥ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትን ወይም በህገወጥ መንገድ የተገኘ ንብረትን ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን የሚመለከት ድንጋጌ በወንጀል ሕጉ ውስጥ ተካቶ ይገኛል። የህጉ ተግባራዊነትሙስናን ለመዋጋት ከፍተኛ ሚና ያለው በመሆኑ ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

8.በመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚፈፀሙ የሙስና ወንጀሎችን ለመከላከል በየተቋቋሙ ያሉ የስነ ምግባር መከታተያ ክፍሎችን ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ሆኖም የበለጠ ቢጠናከሩ ከአሁኑ የተሻለ ውጤታማ ሊሆኑ ስለሚችሉ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው፡፡

9. በጥናቱ ከታዩት ተቋማት ለመረዳት እንደተቻለው በተለያ ሃላፊነቶች ላይ የሚመደቡ ሃላፊዎችና ሰራተኞችን የሃላፊነትና ተጠያቂነት ደረጃና የሚሰሩባቸውን መመርያዎች በግልጽ እንዲገነዘቡ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ በተለይ በመሬት አስተዳደር የአፈፃፀም ችግር እንዳለ ስለሚታይ ጉዳዩን በጥልቀት በማጥናት የማስተካከያ እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል።በተመሳሳይ ሁኔታ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያለው የገንዘብ እንቅስቃሴ በተለይ ከአንድ ቅርንጫፍ ወደ ሌላ ሲተላለፍና፣የደንበኞች ገንዘብ ሲወጣ ያለውን አሰራር፤በጉምሩክ ያለውን የፈታሾች ተጠያቂነት፣የኮንትሮባንድ ጠቋሚን አስመልክቶ ያለውን አሰራር፤በአዲስ አበባም ሆነ በፌደራል ፖሊስ ያለውን የአባላት የሥነምግባር ሁኔታ እንዲሁም በቴሌ ኮሚኒኬሽን ያለውን የሃላፊዎች ተጠየቂነት መመርመር አስፈላጊ ነው። እነዚህ መስርያቤቶች በዘ ያሉ ተከሳሾችን በማስተናገዳቸው ለማሳያነት ተመረጡ እንጂ ብዙ የመንግስት መስርያቤቶች የተለያዩ የሙስና ወንጀሎች ተጋላጭ መሆናቸውን ተከሳሾች ይሰሩባቸው ከነበሩት መስርያቤቶች ዝርዝር ማየት ይቻላል።

በአብዛኛቹ መስርያቤቶች በስልጣን አላግባብ መገልገል፣እምነት ማጉደል፣ጉቦ መቀበል፣ሃሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀት /በተለይ በግዢ ጊዜ/ የመሳሰሉት ሙስና ወንጀሎች በስፋት የታዩ ናቸው። በመሆኑም የመንግስት መስሪያ ቤቶችን አሰራር ከሙስና ነጻ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት መደረግ ይኖርበታል።